**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ( ኢሕአፓ)**

Ethiopian People's Revolutionary Party (EPRP)

ታህሳስ 1/2001 ዓ.ም
December 10/2008

## *60ኛውን አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ቀንን አስመልክቶ የወጣ መግለጫ*

በዛሬው ዕለት ታህሳስ 1(ዲሴምበር 10) 2001 ዓ.ም. አለም አቀፉ ሕብረተሰብ በዓለም ዙሪያ የሰብአዊ መብት ሰነድ የጸደቀበትን ቀን 60ኛ አመት በተለያዩ ቦታዎች ቀኑን እየዘከረ ነው። ይህንኑ ቀን የተለያዩ መግለጫዎችን በማውጣት፣ ልዩ ልዩ የፎቶና የፊልም ኤግዚቢሺኖችን በማዘጋጀት እንዲሁም ጸሎት ከማድረግ አንስቶ ሻማ ማብራትን ያጠቃለሉ ትዕይንቶችንና እንቅስቃሴዎችን ለሕዝብ በማሳየት ዘክረውታል። በነዚህ ዝግጅቶች ላይ ለሰብአዊ መብት መከበር የሚንቀሳቀሱ ቡድኖች፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ሕዝባዊ ድርጅቶች፤ የሲቪክ ማህበራትና በመስኩ በርካታ ተመክሮና እውቀትን ያካበቱ ምሁራኖች ላለፉት ዓመታት እስከዛሬዋ ቀን ድረስ ለሰብአዊ መብት መከበር ሲሉ መስዋዕት የሆኑትን በሕሊናቸው እያስታወሱ፤ አሁንም በአምባገነኖች ለእስር የተዳረጉትን ጽናቱን እንዲያገኙ በመመኘት ነበር ቀኑን ያስታወሱት። በተጨማሪም ያለአግባብ በግልጽም ሆነ በስውር እስር ቤቶች እየማቀቁ ያሉትን የፖለቲካ እስረኞች ሁሉ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ እንዲፈቱ እየጠየቁ፤ በነሱ የተነሳ እየተቸገሩና እየተሰቃዩ የሚገኙትን ቤተሰቦቻቸውንም ለመርዳት፤ የአካልና የመንፈስ ጉዳት ለደረሰባቸውም ልዩ ሕክምናና የመንፈስ እንክብካቤ እንዲያገኙ እርዳታ በማፈላለግና በማሰባሰብ ቀኑን በልዩ ሁኔታ በመዘከር ድምቀት ሰጥተውታል። በተለይም ደግሞ ለሰብአዊ መብት መከበር ጸንቶ መታገልና የሚያስከትለውንም አደጋ በጸጋ መቀበል አኩሪ ተልዕኮ መሆኑን አጽንዖት በመስጠት ትምህርታዊ ግንዛቤ እንዲገኝም ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል። በርግጥም የዘንድሮው አከባበር ልዩ መሆኑን አረጋግጧል።

ለዘንድሮው የሰብአዊ መብት ቀን መከበር ለሥራ እንቅስቃሴ እንዲያገለግል ተብሎ በመሪ መፈክርነት የወጣው ***"ክቡርነትና ፍትህ ለሁላችንም"*** የሚል ነው። ዛሬ ይህ ቀን በዚህ መሪ መፈክር ሲዘከር የትግል ጥሪና የትኩረት አቅጣጫው፤ ሰብአዊ መብቶች ያለምንም ገደብ እንዲከበሩና እነሱ ባዘሉት መንፈስ በመመርኮዝም ማንኛውም ዜጋ ግላዊ ኑሮውን በሰላማዊ መንገድ በመምራት የኤኮኖሚ፤ የባሕላዊና ማህበራዊ ፍላጎቶቹ እንዲሳኩ ጥረት ማድረግ ነው። ከዚህ አንጻር እይታችንን ወደ ኢትዮጵያ ስናደርግ የሰብአዊ መብት ጥበቃና እንክብካቤን አስመልክቶ ሕዝባችን በአሳዛኝና አሰቃቂ ሁኔታ ላይ እንደሚገኝና ወያኔ ሥልጣን ላይ ከወጣ ጀምሮ ላለፉት 17 አመታት - ከአንዱ ዓመት ወደ ሌላው በተሸጋገረ ቁጥር - እየተባባሱ መሄዳቸውን እንገነዘባለን።

ደጋግመን ለመግለጽ እንደሞከርነው የመለስ አገዛዝ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሕግጋትንና ስምምነቶችን ተቀብያለሁ በማለት በራሱ የአገዛዝ ሰነድ ውስጥ ቢያካትታቸውም ከተጻፉበት ወረቀት በላይ ክብደት የሌላቸው ናቸው። 60ኛው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብት ቀን በሚዘከርበት በአሁኑ ወቅት የመለስ አገዛዝ የሚወገዘውና የሚወቀሰው ተቀብያለሁ ያላቸውን የሰብአዊ መብት ሕግጋት የተለያዩ ምክንያቶችን በመፍጠር እየጣሰ አለማክበሩ ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካ መጠቀሚያ ካልሆነ በስተቀር ሕዝብን ለማፈን ሌት ተቀን ሳይታክት የሚሰራ በመሆኑም ጭምር ነው። በቅርቡ የሲቪል ድርጅቶችን በራሱ ሙሉ ቁጥጥር ሥር ለማድረግ ያቀደው ሕግ የሚያመለክተው አንድ ሀቅ ቢኖር ይህንኑ ነው።

በዚህም የተነሳ የመለስ አገዛዝን የሚቃወሙ፤ ለሕዝባቸውና ለሀገራቸው ቀናዒ የሆኑ በሺዎች የሚቆጠሩ በርካታ ሀገር ወዳድ ኢትዮጵያዊያን በበዴሳ፤ ብር ሸለቆ፤ በዝዋይና በሌሎችም የሚስጥር እስር ቤቶች ታጉረው መሰረታዊ መብታቸው ተገፎ ክፉኛ ይሰቃያሉ። በሚደርስባቸው የሥጋና የመንፈስ ስቃይም ከሙታን በላይ ከሕያው በታች ናቸው። ግብረ ሰይል እየተፈጸመ ያለው በኢትዮጵያዊያን ላይ ብቻ ሳይሆን ከባዕድ ሀገር ጠልፎ በእስር ባጎራቸው የውጭ ሀገር ዜጎችም ጭምር መሆኑ ተጋልጧል። ልጆቻቸው እንኳ ሳይቀሩ የአገዛዙ ሰለባ ከመሆን አላመለጡም።

ደብዛቸው እንዲጠፋ የተደረጉት እነ ጸጋዬ ገ/መድህን፤ ስጦታው ሁሴን፤ ብርሃኑ እጅጉ፤ ጌትነት አስናቀ፤ ይስሀቅ ደብረ ጺዮን ሌሎችም በመለስ አገዛዝ የታሰሩ መሆናቸው እየታወቀ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም ስለነሱ ዜና ለመስጠት አሻፈረኝ እንዳለ ይገኛል። በርካታዎች ደግሞ ታፍነው ተወስደው የደረሱበት ያልታወቁት ቁጥራቸውን የሚያውቁት የቅርብ ዘመዶቻቸውና ቤተሰቦቻቸው መሆናቸውን ከመጥቀስ ውጭ በአርምሞ ልብ ይፍጀው ማለቱ የሚቀል ይሆናል። በ1993 ዓ.ም. ከአውሮፕላን ጣቢያ ተጠልፎ በእስር ከቆየ በኋላም ለ10 አመት የእስር ፍርድ የተፈረደበት አበራ የማነአብና እንዲሁም ለፖለቲካ ቂም በቀል መወጫ የተደረገው ታምራት ላይኔም የሙብት እጦትና የፍርደ ገምድል ሰለባዎች መሆናቸውን ነው መገንዘብ የሚቻለው። እንዲሁም ከጥቂት ቀናት በፊት ለሀገር ወዳድ ድምጻዊያንና አርቲስቶች መቀጣጫ እንዲሆን የ6 አመት የእስር ቅጣት የተበየነበት ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ሁኔታም የሚያረጋግጠው ሰብአዊ መብት በመለስ አገዛዝ እንዳሻ የሚጣስ መሆኑን ነው።

ከጾታ አንጻርም ብንመለከት ሴቶች በተለያዩ ማህበራዊና የነጻነት እንቅስቃሴዎች ከወንዶች ያላነሰ አስተዋጽዖ ቢያደርጉም አሁንም እኩልነታቸው አለመረጋገጡ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ጊጂ ባሕሎች እየተበደሉና እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ለጊዜውም ቢሆን ሕይወትን ለማቆየትና የእለት ጉርስ ለወላጆቻቸው ለማቅረብ ሲሉ በለጋ እድሜያቸው ለሴተኛ አዳሪነትና ሰብአዊ ክብርን በሚነካ ተግባር ላይ እየተሰማሩ መገኘታቸው

በትላልቅ ከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠሩም አካባቢ በርካታ ወጣት ሴቶችን ማየቱ ዘግናኝና ልብን የሚያቆስል ነው። ይህ ብቻ አይደለም፤ ወጣቶች በተገቢው መንገድ እንክብካቤ ተደርጎላቸው እንዲያድጉና ተምረውም የሀገራቸውን የወደፊት እጣና ሃላፊነት እንዲረከቡ የማያደርግ ጥረትም የለም። በሥራ አጥነት፤ በአልባሌ ተግባራት መሰማራትና ለበረንዳ አዳሪነት መዳረግ የዚሁ ፖሊሲ ውጤቶች ናቸው። ለሕበረተሰቡ ልዩ ሸክም እንጂ ብሩህ ራዕይ እንዳይሆኑና በዘር ጥላቻ ተበክለውም ብሔራዊ ስሜት እንዳይኖራቸው ያልተቀጠበ ጥረት መደረጉ የአደባባይ ምስጢር ነው።

ብዙሃኑ ሕዝባችን በተለይም በገጠሩ አካባቢ የጤንነት ሥርአት ተጠቃሚ ሊሆን የሚችልበት ሁኔታ አልተመቻቸለትም። ሃሳቡን እንዳይናገር አፉ በጠመንጃ ኃይል ተለጉሞበታል። ብሶቱንና በደሉን በጽሁፍ እንዳይገልጽ እጁ በካቴና ተጠፍሮበታል። ተቃውሞውን በሰላማዊ ሰልፍ ማሰማቱ እንደ አመጽ ተቆጥሮበት በአግዓዚ ነፍሰ ገዳዮች አለርህራሄ ለግድያ የዳረገው በመሆኑ ፍርሃትና ሰቀቀን እንዲሸከም ተደርጓል። የሀገሩ ሉአላዊነት በባዕዳን እንዲደፈር ብቻ ሳይሆን ለም መሬቱን ተቀምቶ በገዛ ሀገሩ ባዳ እንዲሆንና ለሀገሩ እንዳይቆም ተደርጓል። የኑሮ ውድነቱ ከሚሸከመው በላይ በመሆኑ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን ለረሃብ አደጋ አጋልጧቸዋል። የሥራ አጡ ቁጥር ትላልቅ ከተሞችን በማጥለቅለቅ ላይ ይገኛል። ባጠቃላይ ሰብዓዊና ፖለቲካዊ መብቶች በኢትዮጵያ እየተከበሩ አይደሉም።

በመሆኑም ለኢሕአፓ የዛሬው ቀን ሲዘከር፣ እነዚህ መብቶቻችን ያለምንም ገደብ እንዲከበሩና የነጻነታችን ባለቤት በመሆን የወደፊት ዕጣችንን በራሳችን ለመወሰን እንዲያስችለን የፖለቲካ አየር መተንፈሻ ለማግኘት እንድንታገል የትግል ደወል የሚያንቃጭልበት እንዲሆን ነው። የትግል ጥሪው ግቡን እንዲመታ ደግሞ ለችግሮቹ ሁሉ በዋናነት ተጠያቂና መንስኤ የሆነውን የመለስ አገዛዝ ሥርዓትን በቆራጥና መራራ ትግል አስወግዶ በዴሞክራሲ ሥርዓት መተካት አማራጭ የሌለው ነው። ኢሕአፓ ለዚህ የበኩሉን አስተዋጽዖ ያበረክታል እንደእስከዛሬውም ጸንቶ ይታገላል። በሀገራችን የሰብአዊና የዴሞክራሲ መብቶች ያለምንም ገደብ ይከበሩ የሚለው መፈክሩ ዛሬም ሕያውነት ያለው ነውና በትግሉ የሚቀጥልበት ይሆናል። የዛሬው ቀን ዋና መልዕክትም አንድና ይኸው ብቻ ነው።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel . 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France